# የጠቅላይ ሚኒስቴር ሀይለማርያም የዘመቻ ትእዛዝና የአምባገነኖች መመሳሰል

አክሊሉ ወንድአፈረው
ነሀሴ 30፣ 2008
(ሴፐተምበር 5፣2016)

የዛሬ አራት አመት የህወሀትና የኢህአዴግ የበላይ አዛዥና ነዛዥ አቶ መለሰ ዜናዊ ሲያርፉ በቦታቸው የተተኩት አቶ ሐይለማርአም ደሳለኝ በትጥቅ ትግል ካልተሳተፉት የሕወሀት/ኢህአዴግ መሪዎች የተለየ ተመክሮ ያላቸው በመሆናቸው ምናልባት የሀገሪቱን የፖለቲካ አቅጣጫ ቀስበቀስ ከፍጹም ፈላጭ ቆራጭነትና ያአፍሪካ ቀንደኛ አፋኝ መንግስታት ተራ አውጥተው ወደ የህዝብን መብት የማክበር አቅጣጫ ሊያመሩ ይችላሉ የሚል አስተሳሰብ በሰፊው ይሰማ ነበር። "እየሱስ ክርስቶስን የተቀበልኩ ክርስቲያን ነኝ" ብለው መናገራቸው ደግሞ፣ ከሀይማኖተቢሱ መለሰ ዜናዊ የተሻለ ሰብአዊ ርህራሄና ፈሪሀ እግዚአብሄር ያሳዩናል ብሎ የጠበቀው ብዙ ሰው ነበር።

የአራት አመት የጠቅላይ ሚኒስተርነት ሬከርዳቸው ግን ከአቶ መለሰ ጥላስር ሊወጡ አለመቻላቸውን ብቻ ሳይሆን እንዲያውም እየቆየ ተመሳሳይ ባህሪ እያንጸባረቁ መምጣታቸውን እያረጋገጡ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኦሮሚያና በአማራ የተለያዩ ክፍሎች የተነሳውን ህዝባዊ እመቢተኛነት ተከትሎ የሚያሳዩት ጭካኔ የተሞላበት አመራር ደግሞ ፈሪሀ እግዚአብሄር እንዳደረበት ሰው ሳይሆን በሩቅም በቅርብም ከምናውቃቸውን አምባገነን መሪዎች እንደማይለዩ አሳይተውናል። ለግንዛቤ ያክል አንዳንድ ምሳሌዎችን ላንሳ።

## የህዝብን ተቃውሞ የውጭ ጠላት ተቀጽላ አድርጎ የማየት አባዜ

ግብጽን ለ40 አመታት በፈላጭ ቆራጭነት የገዙት ሁሴን ሙባረክም፣ የህዝቡ የነጻነት ፍላጎት የቀሰቀሰውን ተቃውሞ የውጭ ሀይል ፋላጎትን ለማሟላት የተደረገ ሙከራ አድርገው ነበር ያቀረቡት። የቱንዚያው አምባነነን መሪ ቤን አሊም ከስልጣን ከመወገዳቸው ጥቂት ወራት በፊት ህዝብ በነቂስ አደባባይ ወጥቶ ያወግዛቸው በነበረ ጊዜ ባሰሙት ንግግር የህዝቡን ተቃውሞ "በተባበሩት መንግስታትና ሌሎችም ገለልተኛ መንግስታት የተረጋገጠውን እድገታችንን ያበሳጫቸው ጥቂት ግለሰቦች፣ ለሀገራችን ክፉ የሚያስቡ ክፍሎች ያነሳሱት ሁከት ብለው ነበር የገለጹት"
***http://www.lcil.cam.ac.uk/sites/default/files/LCIL/documents/arabspring/Tunisia_2_Final_Speech_President_Ben_Ali.pdf***

አቶ ሀይለማርያምና ድርጅታቸውም እርሳቸው ጠቅላይ ሚኒስቴር ከሆኑ ወዲህም በተመሳሳይ መልክ ሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል "ኢትዮጵያ የራሷ የተፈጥሮ ሀብት እንዳትጠቀም የሚሹ፣ እድገታችንን ለማደናቀፍ የፈለጉ ሀይሎች፣ የትምክተኞች፣ የጠባቦችና" የኤርትራ እጅ እንዳለበት አስመስለው ነው የሚነግሩን። በሽዎች የሚቆጠር ህዝብ ተሰልፎ የሻብያ ቅጥረኛ የእርሰዎ ድርጅት እንጂ የኛ እንቅስቃሴ አይደለም እያለ በይፋ ሲናገር እንኳ ከዚህ ጭፍን አመለካከታቸው አቶ ሀይለማርያምም ሆኑ ህወሀት/ኢህአዴግም ሊወጡ አልቻሉም። ይህ ተግባር አቶ ሀይለማርያምንና ድርጅታቸውን ከሌሎች የታወቁ አምባነነኖች ጋር አንድ ያደርጋቸዋል። እዚህ ላይ ሻቢያ ችግር ከመፍጠር ወደ ሃላ ይላል ወይም ደግሞ ኢትዮጵያ የራሷ የተፈጥሮ ሀብት እንዳትጠቀም የሚሹ ሀገሮች የሉም ለማለት ሳይሆን፣ ያሁኑ የህዝብ ብሶት ህወሀት/ኢህአዴጎች እንደሚሉት የሻአቢያ ተልእኮ ውጤት ሳይሆን የ25 አመታት የስርአቱ አሰቃቂ ግፍ የወለደው መሆኑን ለመቀበል ያለመቻልን አባዜ ነው የሚያሳየው። አቶ ሀይለማርያምና ራሳቸው ባንድ በኩል ስርአቱ "በስብሷል" አስተዳደር የሚባል ነገር በሀገሪቱ ውስጥ የለም " እያሉ እየተናገሩ በሌላ በኩል የህዝብ ብሶት ምክንያቶች ሌሎችን አድርጎ ለማሳየት መሞከራቸው እርሳቸውም ሆነ የሚወክሉት ስርአት የሚጓዝበትን የተምታታ መስመር የሚያመለክት ሲሆን ስርአቱ ለህዝብ ጥያቄወች አመርቂ ምልስ ለመስጠት ብቃት እንደሌለውና ትልቁ ትኩረቱ የስልጣን ጊዜን ማራዘም እንደሆነ ያሳያል።

## የህዝብን መሰረታዊ ተቃውሞ ለማፈን ሰፊ ጭፍጨፋ ውስጥ መግባት

የህዝብ ተቃውሞ የተወሰነ ደረጃን ካለፈ በሓላ ወደነበረበት ለመመመለስ ለአምባ ገነኖች እጅግ ያዳግታል። ይህን ለማድረግ የሚጠቀሙት ባብዛኛው ከፍተኛ የሀይል እርምጃን ነው።
ሳዳም ሁሴን በ1980ወቹ ከኩርድ እና ከሻአ ማህበረሰቦች ከፍተኛ ተቃውሞና የህዝን መነሳሳት ደርሶባቸው ነበር። በተለይም በኩርድሰታን ክፍለ ግዛት የተነሳው ተቃውሞ አይሎ የሀላብጃ (Hallabja) ከተማን ሲቆጣጠር ሳዳምና መንግስታቸው ቀደም ሲሉ ይጠቀሙበት የነበረው የትግል ማኮላሻ ታክቲክ ሁሉ እንደማይሰራ ተረዱ። ይህን ተቃውሞ ለማጥፋት የሀገሪቱን ሰራዊት ሁሉንም

ሀይል ተጠቅሞ አካባቢውን ከተቃዋሚወች እንዲያጸዳ በሰጡት ትእዛዝ በማርች 16፣ 1988 በሮኬት፣ በታንክና በአይሮፕላን ተደገፎ ባካሄዱት ዘመቻ በታሪክ ባስከፊነቱ ሲታሰብ የሚኖር ጭፍጨፋ ፈጽመዋል። በዚህ ዘመቻ በሀላብጃ (Hallabja) ነዋሪወች ላይ የኬሚካል ቦንብ ጥለው ከ3ሽህ እስከ 5 ሽህ የሚገመቱ ኩርዶችን ወዲያውኑ ሲገድሉ ከ7 እስከ 10 ሽህ የሚቆጠሩ ደግሞ አቁስለዋል። በቀጣዮቹ አመታትም ከዚሁ ጥቃት ጋር በተያየዘም በሽወች የሚቆጠሩ ሌሎች ሰዎች ሞተዋል። ያካባቢውን የህዝብ አመጽ ለጊዜውም ቢሆን ማፈን የቻሉት የዚህ አይነት መጠነ ሰፊ ግፍ ፈጽመው እንጂ የህዝብን ብሶት አዳምጦ ፖለቲካዊ መፍትሄ በመፈለግ አልነበረም ።

በሀገራችን ውስጥም አሁን :ለተቀጣጠለው የህዝብ ተቃውሞና እምቢተኛነት የሰለጠነ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በጉልበት ለማንበርከክ አቶ ሀይለማርያም በነሀሴ 24፣ 2008 መግለጫቸው እንዳሉት "ሁሉንም የጸጥታ ሀይሎች ህግ እንዲያስከብሩ አዘዋል"። ይህ ማለት ታንከኛውንም፣ መድፈኛውንም፣ አየር ሀይሉንም ጭምሮ ማለት ነው፡፡ ይህንንም "ትእዛዝ"ተከትሎ እጅግ ብዙ ሰራዊት፣ ታንክና ከባድ መሳሪያ ወደ ጎንደርና ጎጃም የተንቀሳቀሰ ሲሆን በመላ ጎንደርና ጎጃም የብዙወች ደም በመጎረፍ ላይ ነው፡፡

ምርጫ 97ትን ተከትሎ አቶ መለስ በሰጡት ትእዛዝ የተገደሉት ወሀኖቻችን ወደ ሶስት መቶ እንደሚደርሱ ይገመታል። ዛሬ በ2008 ደግሞ በአቶ ሀይለማርያም ይፋ ትእዛዝ ማግስት በጎንደር በጎጃምና በሀረርጌ የተገደሉ ወገኖቻችን ቁጥር እጅግ ብዙ ነው፤ ትላንት ከትላንት ወዲያ በሶማሌና በጋምቤላ ወገኖቻችን ላይ እንደሆነው ሁሉ የዛሬው ጭፍጨፋ ሰለባወች አሰቃቂ እውነታን በቪዲዮና በድምጽ ተቀርጾ ሁላችንም እንድናየው እየተደረገ ነው። ይህ ሁሉ ቀደም ሲል በኦሮሚያ ከተገደሉት ወደ አንድ ሽህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በተጨማሪ ነው።

አቶ ሀይለማርያምና ድርጅታቸው ኢህአዴግ/ህወሀት ይህን በዘር ላይ ያነጣጠረ የግድያ ትእዛዛቸውን ሲያስተላልፉ ምን ያክል ሰው ለመግደል እንደተዘጋጁ ከዚያም መቸ በቃ እንደሚሉ ባናውቅም፣ እስካሁን ባደረጉት ተግባር ግን እርሳቸውና ድርጅታቸው ሳዳም ሳዳምን እንደሚሽቱ ጎጃም ጎንደርና ኦሮምያንም ሀላብጃን እንዲመስሉ ለማድረግ መወሰናቸውን እየተመለከትን ነው።

ይህ ሁሉ የስርአቱን የችግር አፈታት ክህሎት ማነስ ብቻ ሳይሆን በስልጣን ላይ ለመቆየት ምን ያክል ግፍ ለመፈጸም እንደተዘጋጀና ህጋዊም ሆነ የሞራል ብቃት እንደሌለው ያመለክታል።

## ህዝብ ይወደኛል የሚል ቅዥት

የአምባገነን መሪወች አንዱ ትልቅ ስህተታቸው በፍራቻና በትግስት አንገቱን ደፍቶ የሚኖርን ህዝብ ይወደኛል የሚል ትርጉም ሰጥተው ራሳቸውንና ደጋፊወቻቸውን ማታለላቸው ነው። ይህ ያምባገነኖች ባህሪ በተለያዩ ቦታወች ተስተውሏል።
በ አቶ ሀይለማርያም የሚመራው ህወሀት/ኢህአዴግ ለብቻው ተወዳድሮ 99.9% አሸነፍኩ ብሎ የፈጠረውን የራሱን ፖሮፓጋንዳ እንደ እውነት ተቀብሎ እራሱንም ተከታዮችንም ሲያጭበረብር ቆይቷል። የስርአቱ ቁንጮወች ባንድ በኩል ህዝቡ እጅግ ዘግናኝ በሆነ ሙስና የሙብት ረገጣ፣ የህግ ጥሰት ወዘተ እንደተሰቃየ እያመኑ ዘወር ብለው ደግሞ ህወሀት/ ኢህአዴግ አሁንም ህዝብ "ያቀፈው መንግስት" እንደሆነ ራሱን ያታልላል። በየቦታው የህዝቡን ልጆች የሚገድለው፣ ባደባባይ የሚረሽነው፣ ወዘተ ለራሱ ለህዝብ ነው በሚል ቅዣት ራሱን ያጭበረብራል። ንብረት የምንጥቀው፣ ከመኖሪያ የምናፈናቅለውም ለራሱ ለህዝቡ ስል ነው ይላል።

በኦሮሚያ ለ10 ተከታታይ ወራት ሰፊ ተቃውሞ እየታየ፣ አቶ ሀይለማርያም የሚመራው ህወሀት/ኢህአዴግ ሰላም አስፍነናል ይላል። በመላው ጎንደርና ጎጃም የህዝብ እምቢተኛነት ተቀጣጥሎ በጎንደር ብቻ 100 ሽህ ሰው የተቃዎሞ ሰልፍ ሲያካሂድ "ጥቂት" ትምክተኞች ብሎ ይነግረናል። ህወሀት/ኢህአዴግ ካንድ ሳምንት በፊት በአቶ ሀይለማርያም ሰብሳቢነት ባካሄደው ጉባኤ መጨረሻ ባወጣው መግለጫ ሳይቀር አሁንም ህዝብ እደሚደግፈው ይናገራል።
የሊቢያው መሀመድ ጋዳፊ፣ የግብጹ ሙባረክና ሌሎችም አምባገነኖች በስልጣናቸው መጨረሻ ሰሞን ተመሳሳይ "ህዝቤ ይወደኛል" የሚል ቅዥት የተቀላቀለበት ንግግር ያሰሙ እንደነበር የሚታወስ ነው።ዛሬ ከህወሀት/ኢህአዴግ መሪወች የምንሰማውም ተመሳሳይ የጣር ጩኸት ነው።

ይህ ሁሉ ስርአቱ የመግዛት አቅሙ እንደዛለ ብቻ ሳይሆን በመሬት ላይ የሚገኘውን እውነታ ለማገናዘብም የማይችልበት ሁኔታ ላይ እንደደረሰና ከዚህ በሁዋል በስልጣን ላይ መቆየቱም ለሀገር ደህንነት ታላቅ አደጋ እንደሆነ ያመላክታል። :

## የራሱን ጥላ የማያምነው ህወሀት/ኢህአዴግና ለእርድ የተዘጋጁት ባለስልጣኖች

ጠቅላይ ሚኒስቴር ሀይለማርያም የሚመራው ህወሀት/ኢህአዴግ፣ ህዝቡንና ተቃዋሚውን ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ያሉትን "አጋሮቹን " ሳይቀር በጥርጣሬ ማየትን ከጀመረና አላምናቸውም ካለ ውሎ አድሯል። ቀደም ሲል የኦህዴድን አሁን ደግሞ የብአዴንን መሪወችና አባላት በየቀኑ በአሳፋሪ ክስ በአደባባይ ሲወነጅላቸው፣( ኪራይ ሰብሳቢ፣ ጠባብ፣ ትምክተኛ ወዘተ ሲሏቸው) "ራሳችሁን አጋልጡ" እያለ ሲያሰፈራራቸው፣ ሲያዋርዳቸው ወዘተ በሰፊው ይታያል።
የሰሜን ኮርያ አምባገነኖች እና ሟቹ ሳዳን ሁሴን በተደጋጋሚ እንዳሳዩት ህወሀት/ኢህአዴግም በተደጋጋሚ እንዳደረገው ሁሉ

አሁንም በአዲስ መልክ አጋሮቹን ተራ በተራ አኝኮ ለመትፋት ተዘጋጅቷል። እንደ ተራ እቃ ተጠቅሞባቸው ሊውረውራቸው እንደሚፈልግ በግልጥ እየተናገረ ነው። ይህንን እያወቁ ለእርድ ወደቄራ እንደሚሄድ በሬ አይናቸውን አፍጥጠው ይጠብቃሉ ወይንስ አማራጫቸውን በጊዜ ይፈትሻሉ የሚለው የሚታይ ይሆናል። ነገሩ ልብ ያለው ልብ ይበል እንደሚባለው ነው።

## ማጠቃለያ

አንዳንዶች ጠቅላይ ሚኒስቴር ሀይለማርያምን ከጀርባ ሆነው የሚያሽከረክሯዋቸው የህወሀት ሰወች ናቸው፣ ስለዚህ አርሳቸው ምን ያድርጉ? የሚል መሟገቻ ያቀርባሉው። በርግጥ አቶ ሐይለማርያም የተቀላቀሉት ቡድን እጅግ አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ባንድ ወቅተ "እኔ ምንአባቴ ላድርግ ብላችሁ ነው" ሲሉ መደመጣቸው ይታወሳል፡፡ ሆኖም ግን ጠቅላይ ሚኒስቴሩ በእድሜም በትምህርትም የገፉና ብዙ አለም አቀፍ መሪዎችንም አግኝተው የተመካከሩ፣ እጅግ ብዙ ግንኙነት ያላቸው ግለሰብ ናቸው። ሰለሆነም በማያምኑበት ተግባር ላይ (ያውም በጭካኔ ተግባር) ሊሳተፉ የሚያሰገድዳቸው ምንም ጉዳይ የለም። ስልጣኑ አጓጉቷቸው ካልሆነ በስተቀር የማይመስላቸውን ያውም ህዝብ ላይ ሰራዊት ማዝመትና ጭፍጨፋ መፈጸምን የመሰለ ታላቅ ጭካኔ የተሞላበት ውሳኔ ተቀብለው ማሰተጋባትና ተግባራዊ ማድረግ በምንም ሰበብ ቢሆን ተቀባይነት የለውም:፡

ጠቅላይ ሚኒስቴሩም ሆኑ ሌሎች ባለስልጣኖች እምቢ ሰለማለት ደግሞ ከቀድሞው ፐሬዚደንት ከዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ሊማሩ ይገባል። አቶ መለሰ የአምባገነን ባህሪያቸው እጅግ እያየለ ሲሄድ ነበር ዶክተር ነጋሶ ፣ " ምነው ደርግ ደርግ ሸተቱኝ" ብለው በትክክል የሚሰማቸውን የነገሯቸው። በርግጥ ዶክተር ነጋሶ ያንን ተከትሎ ከስልጣናቸው ተባረዋል፤ ከሀገር ፐሬዚዳንትነት ተነስተው ተራ ሰው ሆነዋል። ሆኖም ግን ንጹህ አእምሮ፡ መልካም ሰብእናና ጽኑ መንፈስ እንዳለቸው ሕዝብም መስክሮላቸዋል። በርግጥ ከቤተመንግስት ተወግደዋል። በህዝብ ልብ ውስጥ ግን ታላቅ ቦታን ይዘዋል።ዶክተር ነጋሶና ቤተሰቦቻቸው ዛሬ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል አንገታቸውን ቀና አድርገው፣ እርሰዎ ተብለው እንደተከበሩ መንቀሳቀስ ይችላሉ። በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ ጥላቸውን አይፈሩም።

ጠቅላይ ሚኒስቴር ሀይለማርያምም፣ የተቀመጡበት ወንበርና፣ ከስልጣን ጋር የሚመጣው ሀላፊነት ምን ያክል ከባድ እንደሆነ  በማገንዘብ ለሀገር፣ ለህዝብና ለራሳቸው ታሪክ የሚሆነውን በጊዜ ሊያደርጉ እንደሚገባ መናገር ድፍረት አይሆንብኝም። አሁን በይፋ የሚታየው ድርጊታቸው ግን ለራሳቸው አእምሮም ሆነ ለታሪካቸው፣ ለሀገርም ሆነ ለህዝብ በፍጹም አይበጅም። በይፋ የሚታየው ተግባራቸው የሚያመለክተው ለውጥ አጋችነትን እንጂ ለውጥ ፈላጊነትን አይደለም። የሀገሬ ሰው ሲከፋው እንደሚለው፣ ወይ ውረድ ወይ ፍረድ።

**http://www.ethiopanorama.com**